

## 16

# ሁሉን ችሎ
# የማለፍ ምስጢር

16-1

ጳውሎስ በፊሊጵስዮስ ላሉት ክርስቲያኖች ወህኒ ቤተ በነበረበት ጊዜ በጣም የሚያጽናና ደብዳቤ ጻፈላቸው። መልዕክቱም "ሁሉን በሚያስችለኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" (ፊሊ. 4፥13) የሚል ነበር። ለፊሊጵስዮስ ምዕመናን የተጻፈው የሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤ በረከት የሞላበት በዘመናት ሁሉ ብዙ አማኞችን ያጽናናና ብርታትን የሰጠ ነው። ሐዋርያው ከራሱ ባልመጣ (ባልመነጨ) ኃይል የተለያዩ መጥፎ ሁኔታዎች ሲደርሱበት ሳይሸነፍ መኖር የቻለ መሆኑን ደብዳቤው በግልጽ ያመለክታል። በአሁኑ ዘመን ያለነው ክርስቲያኖች ያለበደላችን (ያለጥፋታችን) ካለአግባብ ተይዘን ብንታሠር ነጻነት የማግኘት ዕድላችን የመነመነ ቢሆን፥ ከእስር ቤት ሆነን ለወዳጆቻችን የምንጽፈው ደብዳቤ ምን ዓይነት ይሆን? ለማጉረምረም፣ ለማዘን፣ ስለ ክርስቶስን ስንል ምን ያህል ታላቅ መከራና ስቃይ እደደረሰብን ለመጻፍና ለመናገር በቂ ምክንያት ይሆንልን ነበር። የሐዋርያው ጳውሎስን መልዕክት ስናነብ ምንም ዓይንት ማጉረምረማን መበሳጨት አናይም። "ያለአግባብ ታሥሬ እሰቃያለሁና እባካችሁን ጸልዩልኝ" በማለት ተጨንቆ የሚያስጨንቅ ደብዳቤ አልጻፈም። በምትኩ ግን የአማኞችን እምነት የሚያጠነክርና የሚያዳብር ደብዳቤ ጻፈ። ጳውሎስ በመሸነፍ ፈንታ በድል መመላለስ የሚችልበትን ዘዴና ምስጢር መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት እንደነበር እናያለን። ጳውሎስ አሳዛኝ የነበረውን የእሥር ቤት ኑሮውን ብዙዎቻችንን እስኪያስደንቀን ድረስ በደስታ የተቀበለው ስለሆነ፥ በመከራው ከመጎዳት ይልቅ ትልቅ የክርስትና ሕይወት ልምምድ እንዲሆነው እንደተጠቀመበት እናያለን።

"ደግሞም ይህን የምለው ስለ ኑሮዬ ችግር በመበሳጨት አይደለም፤ ምክንያቱም ማጣትንም ሆነ ማግኘትን ተለማምጃለሁ፤ እንዲሁም በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ስላለፍኩ "ያለኝ ነገር ይበቃኛል" የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ። ክርስቶስ በሚሰጠኝ ሁሉን ነገር ማደረግ እችላለሁ" (ፊሊ. 4፥11-13)። ጳውሎስ "ማጣትን ተለማምጃለሁ" ሲል በችግር ውስጥ ያለፈ መሆኑን ይገልጻል። ይቀጥልና "ማግኘትን ተለማምጃለሁ" ይላል። ለብዙዎቻችን አስቸጋሪ የሚሆንብን ማጣት ሳይሆን ማግኘት ነው። በጥጋብ ዘመናችን በቀላሉ ልባችንና ሃሳባችን ከእግዚአብሔር ይሸሻል። በድህነት ያወቅነውን አምላካችንን በብልጽግናችን ዘመን እንረሳዋለን። ጳውሎስ ግን የዚህ ችግር አልነበረበትም። ይቀጥልና "በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ማለፍን ተለማምጃለሁ" ይላል። ይህን የጳውሎስ አነጋገር ስንሰማ እኛ የዘመኑ ክርስቲያኖች የሌለንን ዓይነት እምነት ጳውሎስ እንደነበረው በግልጽ እናያለን። "በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ማለፍን ተምሬአለሁ" በማለት በሙሉ ልባችን መናገር እንችል ይሆን? ብዙዎቻችን ቃላቱን በአፋችን እንናገረው እንጂ በመከራና በችግር ውስጥ ስናልፍ ሁኔታዎችን እንደ አመጣጣቸው በትዕግሥት በማለፍ ፈንታ በማጉረምረምና በማዘን ሕይወታችን እንዲመራ እናደርጋለን።

# ጳውሎስ ያለፈባቸው ሁኔታዎች

ጳውሎስ "በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ማለፍን ተምሬአለሁ" ሲል ለመናገር ብቻ ያለው ሳይሆን በእርግጥም ልዩ ልዩ ክፉ ሁኔታዎች ደርሶበት አልፎ ነው። ያለፈበትን ሁኔታ ሲዘረዝር እንዲህ ይላል፥

1. **"ሠላሳ ዘጠኝ ሠላሳ ዘጠኝ ጅራፍ አምስት ጊዜ በአይሁዳዊያን ተገርፌአለሁ"** (2ኛ ቆሮ 11፥24)።
   በአይሁድ ሕግ የመጨረሻውና ከፍተኛው ግርፋት 39 ጅራፍ ነው። በጳውሎስ ላይ የደረሰው ግርፋት ማንኛውንም ሰው ቢሆን አካል ስንኩል ዓይነ ሥውር እንዲሁም እስከሞት ድረስ ሊያደርሰው የሚችል ነበር። የሚገረፈው ሰው ግርፋቱን የሚቀበለው ራቁቱን ሆኖ ነው። በእያንዳንዱ የጅራፍ ዘርፍ ላይ ብረት ያለበት ስለሆነ አንዱ ጅራፍ እንኳን በሰውየው እርቃነ ሥጋ ላይ ሲያርፍ ቆዳውንና ሥጋውን እየሰነጠቀ ይገባል። ጳውሎስ ይህን ዓይነት ግርፋት አምስት ጊዜ ደርሶበታል። የጳውሎስ ጀርባ ቢታይ ጠባሳ የሞላበት ይሆን እንደነበር እንገምታለን። እዚህ ላይ ማየት የሚያስፈልገን የቅጣቱን ኃይለኝነት ሳይሆን፥ የጳውሎስን ትልቅ ትዕግሥትንና ጽናትን ነው። ጳውሎስ ሁኔታውን እንዳለ ተቀብሎ በደስታ የማለፍ ልዩ ትምህርትን አግኝቶ ነበር።

2. **"ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ"**
   ጳውሎስ የጀርባ አጥንቱ እስኪናጋ ድረስ በዱላ ተቀጥቅጧል። የጀርባ ሕመም ያለባቸው ሰዎች በዘመናችን ምን ይህል እንደሚሰቃዩ እናውቃለን። ጳውሎስ ያ ሁሉ ዱላ በጀርባው ላይ ሲወርድበት መነሳት የማይችል በሽተኛ ሆኖ ሊቀር ይችል ነበር። በዚህ ሁሉ መከራ ግን ጳውሎስ በድል አድራጊነት አሸንፎ የሚወጣበት ልዩ ምስጢር ነበረው።

3. **"አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ"**
   በሐዋርያት ሥራ 14፥19-20 ላይ በጳውሎስ ሕይወት አስደናቂ ተአምር እንደተደረገ እናነባለን። አይሁዳውያን ሕዝቡን በጳውሎስ ላይ አሳድመው በድንጋይ ወገሩት። የሞተም መስሏቸው ጎትተው ከከተማ አወጡት። ደቀ መዛሙርቱ በዙሪያው በቆሙ ጊዜ ግን ተነስቶ ወደ ከተማ ገባ በማግስቱም ረጅም ጉዞ በእግሩ ተጉዞ ደርቤ ደረሰ። ይህን ስንመለከት ጳውሎስ ክፉውን ታግሶ የሚያልፍበት ልዩ ኃይል እንደነበረው እንገነዘባለን። ጳውሎስ የደረሰበትን ልዩ ልዩ መጥፎ ሁኔታዎችን ሲዘረዝር እንዲህ ይላል "ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና አንድ ቀን በባህር ላይ ነበርሁ። በጉዞዬ ብዛት የወንዝና የጎርፍ የሽፍቶች አደጋ ደርሶብኛል፤ በከተማና በበረሃ በባሕርም አደጋ ደርሶብኛል። ብዙ ሥራና ድካም ነበረብኝ። ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ በረሀብና በውሃ ጥም ተጨንቄአለሁ፤ ብዙ ጊዜም የምግብ እጦት ደርሶብኛል፤ ብርድና መራቆትም ደርሶብኛል" (2ኛ. ቆሮ. 11፥25-27)። ጳውሎስ ያለፈበትን የሕይወት ልምምድ ስንመለከት በአካል፣ በመንፈስና በነፍስ መሰቃየትን ያወቀ ሰው እንደነበረ እንረዳለን። ማንኛውንም ሁኔታ ተቀብሎ ማለፍ እንዴት እንደሚ ችል ትክክለኛ ትምህርት ሊሰጠን የሚችል ሰው ቢኖር በሕይወቱ ተለማምዶ ያየ፥ ከጳውሎስ የተሻለ ሌላ ሰው ይኖራል ብለን አንገምትም። ጳውሎስ የሚያገጥመውን አስከፊ ሁኔታዎች ሁሉ አሸናፊ ሆኖ እንዲያልፍ ያደረገው ነገር ምንድነው? መልሱ፥ ጳውሎስ ከጌታው ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት ስለነበረው ነው። በውስጡ የነበረው ኃይል ከራሱ የመነጨ ሳይሆን ከክርስቶስ የተቀበለው ኃይል ነበር። ብዙዎቻችን "ክርስቶስ ኃይላችን ነው" ብለን በቃላት እንጥቀሰው እንጂ በሕይወታችን ግን ሲሆን አይታይም። "ክርስቶስ በሚሰጠኝ ኃይል ሁሉ ነገር ማድረግ እችላለሁ" ሲል ጳውሎስ የኃይሉ ምስጢር ክርስቶስ እንደሆነ ሲመሰክር ነው።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**